# ከኢትዮጵያ ሠራዊት (የቀድሞ)

ሚያዝያ 19 ቀን 2012 ዓ ም

*የሁለት ዓመት የግፍ ጉዞ*

*ግልጽ ደብዳቤ ለዶክቶር አቢይ አህመድ*

*አዲስ አበባ፤ኢትዮጵያ*

*ከኢትዮጵያ ሠራዊት(የቀድሞ)*

እንደሚታወቀው አንድ በሕዝብ የተመረጠ መሪ የሚተገብራቸው ከሞላ ጎደል የሕዝብን ፍላጎት የሚያሟላ መሆን እንዳለበት ለእርስዎ የሚነገር አይደለም። አንድ መሪ በሚያስተዳድረው ክልል ውስጥ ለሚገኙ ሁሉ ተጠሪ ነው፡ እንኳንስ ሰውና እንሣሣ ቀርቶ ዛፉንና አፈሩን የመጠብቅ ኃላፊነት እንዳለበት ለእርስዎ ተዓምር ሊሆን አይገባም።

ከላይ የተጠቀሰውን መንደርደሪያ በመንተራስ በማኅበር የተደራጀ የኢትዮጵያ ሠራዊት(የቀድሞ) ከርስዎ ከአንድ መሪ የማይጠበቅ ድርጊቶች ሲፈጸሙ በኃዛኔታ እያየን ነው። ሥህተቱ ከዛሬ ነገ ይሻሻል ይሆናል የሚል ተስፋ ሰንቀንም እስከዛሬ ቆይተናል፣ ማኅበራችን የየዕለቱን በጎ ሥራዎንና ሥህተትዎን ገምግሞ ከአንድ ውጤት ላይ ከመድረሱ በፊት ይህች ማስታወሻ እንዲደርስዎት ሲወስን እርስዎ በኢትዮጵያ ሕዝብ እና በአገር ላይ የፈጸሙትን በደልና ግፍ ጥቂቱን ብቻ በማስታወስ ነው። እርስዎ የኢትዮጵያን ሕዝብ ለማስተዳደር በሕዝባችን ይመረጡ ወይም በአራድነት ሥልጣኑን ይቆጣጠሩ በተጨባጭ ባናውቅም የሕዝብ ውክልና የሌለው መቶ በመቶ ምክር ቤቱን የተቆጣጠረ የወያኔ ታማኞች እንደሰየሙዎት ሲወራ ተሰምቷል። ጉዳዩ የመሰየም ወይም የመሾም አባዜ ሣይሆን እርስዎ በሕዝባችንና በአገራችን ላይ ያደረሱትና በማድረስ ላይ የሚገኙትን ክፋት በዝምታ የምናየው አይደለም። ዶክቶር አቢይ ጥፋትዎን በሹክሹክታ የምናወራው ሣይሆን ገሃድ የወጣውን ግፍ በመጥቀስ ነው፣ እጅዎ በኢትዮጵያዉያን ደም ተበክሏል፥ ይህ ደግሞ በምስጢር የተወራ ወይም የተንሾካሾከ ሣይሆን መላው ዓለም ያወቀው ሲሆን ከፊሎቹን በሚቀጥለው መሥመር ለመግለጽ እንገደዳለን፥

1) ኢንጂኔር ስመኘው በቀለ በጠራራ ፀሃይ መገደል እጅዎ እንዳለበት ሕዝባችን በአደባባይ እየመሰከረ ነው

2) ለገ ጣፎ የአማራ ሕዝባችን ቤታቸው ሲፈርስ ለከንቲባዋ የስልክ ትዕዛዝ መስጠትዎን ከንትባዋ መስክራለች፣

3) ቡራዩ ከአሥር ሺህ በላይ የጋሞ ሕዝብ ሲፈናቀልና ሲዘረፍ ትዕዛዝ ለኦሮሚያ ክልል እንደሰጡ ተበዳዮቹ ይናገራሉ፣ ስለሆነም ለተፈፀመው በደልና ዘረፋ ተጠያቂ ነዎት።

4) በጂጂጋ ቤተክሪስቲያን ሲቃጠል እና ከ36 ምዕመናን በላይ ሲታረዱ በዝምታ አልፈውታል። ቤተክህነት ስለጥፋቱ ቢጠይቆት መልእክቱን ያመጡትን አባቶች ከማንጓጠጥም አልፈው<<እኔ ቤተክርስቲያን አላቃጠልኩም፣ጠባቂም ስላልሆንኩኝ ይቅርታም አልጠይቅም>> በማለት አባቶችን አዋርደው አባርረዋቸዋል፣ ከዚያ ቀን ጀምሮ እርስዎ የኦርቶዶክስ ጠላት መሆንዎን መላው የኦርቶዶክስ አማኞች አረጋግጠዋል፣ በተጨማሪም የኦርቶዶክስ አማኞች ሰላማዊ ሠልፍ እንዳይወጡም ከልክለዋል፣ ዶክቶር አቢይ በእርስዎ ምስጢራዊ አመራር ስጪነት የታረዱና የተቃጠሉ ቀሳውስትና ኦርቶዶክስ አማኞች ደም በእጅዎና በግንባርዎ ላይ እያቃጨለ ስለሆነ ዉርደትና ዉድቀትዎ ከመለስ ዜናዊ የገደደ እንጂ የሚያንስ እንዳልሆነ እሙን ነው። በዚህ ደብዳቤያችን የማሳስቦት እርስዎ በሕዝባችን ላይ ለፈፀሙት እሮሮ እንደሚጠየቁ ስንጠቁሞት ካለምንም ተነስተን አለመሆኑን ይረዱ፥ የበደለ ይክሳል፣የተበደለ ይቅር ይላል የሚለውን የአበው ምክር ሣናጤነውም አይደለም ሁሉንም መርምረናል፣ ወሽካታ

ዲስኩሮን አጢነናል፣ራስዎ ልብ ገዝተው ከተመለሱ እሰዬ አገርን ለማፍረስ የጋሸበ ልብዎ አደብ ካልገዛ« ጨው ለራስህ ሲትል ጣፍጥ» የሚለውን ብህል አከለንበት እንቀጥላለን።

5) የአዲስ አባባ ወጣቶች ምንም ሣይበድሉ ወደ ጦላይ አስወስደው ያሳሰሩዋቸውና በወባ ወረሪሽኝ የሞቱት ወጣቶች ወላጀቻቸው ወደ እግዚአብሔር እየጮሁ ናቸው፣ ስለሆነም በከንቱ ላፈሰሱት የእምቦቃቅላ ወጣቶች ደም ተጠያቂ ነዎት። እንዲሁም ወታደሮችዎ ቶርች ሲያደርጓችው ሽባ ለሆኑት ወጣቶች ተጥያቂ ራስዎ ነዎት፥

6) በየትኛውም የኢትዮጵያ ክፍል ለተፈጸመ መፈናቀል በግንባር ቀደም ተጠያቂ እርስዎ ነዎት። ሚስትና ልጆቹ የተገደለበት ኢትዮጵያዊ  የእርስዎን ሚስትና ልጆችዎን ከመበቀል ወደ ኋላ እንደማይሉም እርግጠኞች ነን « ያለፈ አልፏል ለወደፊት አይደገምም»የሚል መንግሥት እንደማይመጣ  ይረዱ፣« ወያኔ ለበደለው እኔ ይቅርታ እጠይቃለሁ»ብለው ከወያኔ ምክር ቤት ስብሰባ ላይ ፎክረው ነበር፥ለመሆኑ ማን ወክሎት ነበር??

7) ቁጥራቸው ከ20 በላይ የሆኑ ተማሪዎች ከደምብዶሎ ዩኒቨርሲቲ ታፍነው ደብዛቸው ስለጠፉ ተማሪዎች ተጠያቂ እርስዎ ነዎት፣ የለገጣፎ ቤት ሲፈርስ አልሰማሁም  ጆሮዬን ይድፈነው፣ ዓይነን ግንባር ያድርገው እንዳሉ እንደማይሆን አይገምቱ፣ጃን መሮ ላደረገው ጥፋት ተጠያቂ እርስዎ መሆኑንም አይዘንጉ፣ ምክንያቱም የአገሪቱ መሪ ነዎትና።

8) ጀዋር ሻሸመኔ ይሄዳል ተብሎ ደጋፊዎቹ ተሰብስበው አንድ የመንግሥት መኪና ሲያቃጥሉ አሽከርካሪውን በዛፍ ላይ ቁልቁለት ሰቅለው ገድለውታል፥ ለዚህ ኢትዮጵይዊ ዜጋ ያለ አበሳው ለፈሰሰው ደም ተጠያቂ ማነው ነው ቢባል ያለ ምንም ማመንታት የአገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስተር ዶክቶር አቢይ ናቸው፣ በአሰላ የአራት ሕፃናት እናት አራስ መምህርት ኦርቶዶክስ ስለሆነች የጀዋር ደጋፊዎች ጡቷን ቆርጠው ሲግድሏት በቭዲዮ ተቀርፆ ታይቷል፡ለዚህ ተጠያቂ እርስዎና መንግሥትዎ ነው።

9) እርስዎ በፓርላማ ስብሰባ ላይ በተናገሩት ጀዋር ሌሊት ተከብበአለሁ ብሎ በመወትወቱ ቁጥሩ የማይታወቅ ኢትዮጵያውያን ያለ ምንም ጥፋት ተጨፍጭፈዋል ፣እርስዎ ከሣምንታት በኋላ ለይስሙላ ወደ ቲቪመስኮት ብቅ ብለው 86 ሰዎች እንደተገደሉ ተናግረዋል። ይሁንና ለ86ቱ ሕይወትተጠያቂ ማነው ቢባል ዶክቶር አብይ ነው።

10) በወለጋ ለተዘረፈው 18 ባንኮች ተጥያቂ ማነው ቢባል ዶክቶር አቢይ እንደሆኑ ማንም የሚመስክር ነው።

11) አገሪቱ በእዳ ተወጥራ ባለችበት በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያን ሲያደሙት ለኖሩት ጽንፈኞች መደመር በሚል የዋልጌ ፍልስፍና ወደ አገር አስገብተዋቸው በዉድ ሆተሎች በማኖር በአገራችን ላይ ከፍተኛ የምጣኔ ሀብት ዉድወት  እያደረሱ ስለሆኑ  ጊዜው ሲፈቅድ በሕግ ፊት እንደሚቀርቡ እርስዎም አያጡትም።

12) ጀዋር ለሚባል ዓለም አቀፍ ወንጀለኛ ከ10  እስከ 12 ለሚደርሱ አጃቢዎች ያለ ምክር ቤቱ ውሳኔ ደመወዝ እንዲከፈል በማድረግዎ ለወደፊቱ በሕግ እንደሚጠየቁ መዘንጋት የለቦትም።

13) የኢትዮጵያ ጠላት ከሆነች ከግብፅ ጎን ተሰልፎ ከውስጥ በጥባጭ የሆነ ጀዋር መሐመድን ከሕግ ፊት ባለ ማቅረብዎ በወንጀል ተጠያቂ ነዎት።

14) ተከባብሮና ተፋቅሮ የኖረውን ሕዝባችንን ለመከፋፈል ባለና ሐረር ሲጎበኙ ከአንድ መሪ የማይጠበቀውን ወራዳ ድስኩር በመናገርዎ ተጠያቂ ነዎት።

15) ሰኔ 15ቀን 2011 ዓ ም በአማራ ክልል ለተፈፀመ እልቂት በቀጥታ ተጠያቂ ነዎት፣ ያለበደላቸው ለታሰሩትና ቶርች ለተደረጉትም ንጹሃን ኢትዮጵያውያን በፈፃሚነትና በአስፈፃሚነት ተግባር ተጠያቂ ነዎት።

ዶክቶር አቢይ ያለፈው የሁለት ዓመት የሦቆቃ አገዛዝዎ ሕዝባችንን በጎሣና በቋንቋ ከፋፍለው የሚያጋድሉትን እኛ የኢትዮጵያ ሠራዊት  ከዳር ሆነን የምመለከተው ይህ እኩይ ዘመቻዎ  ከዛሬ ነገ  ያበቃ ይሆናል ብለን እስካሁን ስንጠባበቅ ቆይተናል፥ ግን እርስዎ ሕዝባችንን ንቀው መግደሉንና ማፈናቀሉን አጠናክረው ቀጥለውበታል። ዶር ሕዝባችንን በመከፋፈል የነደፉትን የወረደ መርሃ ግብር  እኛ በቀላሉ አንመለከተውም፥ ከሁሉም ደግሞ የአማራን

ሕዝብ ለማጥፋት የሚቃዡት የቀን ሕልም ፋይዳ እንደሌለው እንዲያውቁት አበክረን እንገልጽሎታን----------ቢያከብሩት የተፈራ ይመስለዋል ይላሉ አበው ሲተርቱ።

የአማራ ሕዝብ የተግባር ኢትዮጵያዊ ነው፣ ከጥንት ጀምሮ ከሩቅ ወራሪዎች፥ ከቅርብ ተስፋፊዎችና ከሥልጣን ጥመኞች ጋር ተፋልሞ ኢትዮጵያን እንዳቆያት እርስዎ አያጡትም ብለን እንገምታለን ግምታችን ስሕተት ከሆነ ከዛሬ ጀምሮ እንዲያውቁ እንጠቁሞታለን።

ዶክቶር አቢይ እርስዎ እንደ ዮዲት ጉዲት የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ለማጥፋት ታጥቀው እንደተነሱ ኦርቶዶክሳውያን ቀደም ብለው አውቀዋል፥ አስተዳደርዎ በዚህ አካሄዱ የትም የትም እንደማይደርስ ስለሚታወቅ የሚጨነቅ የለም።

ዶ ር አቢይ እርስዎና መሰሎችዎ የኢትዮጵያን ለማጥፋት የማይምሱት ጉድጓድ ፣የማይፈነቅሉት ድንጋይ የለም፥ ግን አይሳካሎትም፣ እንኳንስ እርስዎ ሲጀመር አንስተው በመፈንቅለ መንግሥት የታጀቡ ቀርተው እነ ሬጋን እንኳን አልተውሳካላቸውም። ትልቁ አጀንዳዎ ኢትዮጵያ የምትባል አገር ከነታሪኳ ማጥፋት ሲሆን፥ ይህን ለመተግበር ደግሞ ኦርቶዶክስን ማጥፋት፥ኦርቶዶክስን ለማጥፋት ደግሞ አማራን ማጥፋት የሚለው የጥፋት መርሃ ግብርዎ ቀደም ተብሎ ስለታኘከ በከንቱ ወታደርዎን ባያስፈጁ ይበጃል እንላለን።አማራን በተወለደበት ቄዬ በጠመንጃ መግዛት አይሞከርም። ፋኖ የሕዝብ ልጅ ነው፣ኃይሉ ውቅያኖስ ነው፣እርስዎ የሚመኩበት የመዋጮ ወታደር የጭልፋ ውሃ ነው።

ለኢትዮጵያና ለባንዲራዋ የቆመ ሁሉ ፋኖ ነው፣ለዚህ ነው እኛም ፋኖ ነን የምንለው።

የአማራ ሕዝባችን ለኢትዮጵያ መንግሥት ግብር ይከፍላል፥ በገንዘቡ ለልዩ ልዩ አስተዳደራዊ ሥራ ሲውል ከፊሉ ለመከላከያ ኃይል ይመደባል፥ለመከላከያ የሚመደብው በጀት ለአገር ደኅንነት ጥበቃ ሆኖ ሣለ የእርስዎ አመራር ግን በተቅራኒ ወገንን ሊጨፈጭፍበት እየጣረ ነው። ዶር አቢይ የእርስዎ ወታደር ኢትዮጵያን አሰዳቢ ሴት በዘነዛና ጉሩበውን ብላ ጠመንጃ የምትቀማው ነው።

ክቡር ዶር በጣም ብዙ የጎንደር ተወላጆችን ከአዲስ አባባ አስጭነው ወደ አማራ አገር አስወስደዋል፥ ምን ማለትዎ ነው? አዲስ አባባ የአማራ አገር አይደለም ማለት ነውን? ወሰኑ ዲዶ ያለዉን እንስታውሶት!!

« ማሲን ጋማ ላፋ ንምባቱ ተልባ ፋጫፋታ ታቲ!!

«ቶኮ ኛቴ ቶኮ ንደቡ ውል ጋጋላፋታ ታቲ!!

አጭር ትርጉሙ አንዱ በልቶ ሌላው ጦሙን አያድርም፥ ሁላችንም ተያይዝን እንጠፋታለን ነው።

ክቡር ዶር ጉዳዩን እናሣጥረውና እርስዎ የአማራን ሕዝብ በታንክና በአውሮፐላን ለመደብደብ እግረኛ ጦር ወደ አአማራ ክልል ማስገባትዎ በግብር እይታየ ነው፣ ሐቁን ለመናገር ኢትዮጵያ በደቡብ፣ በምሥራቅ፣በሰሜን ተከብባ በነበረ ጊዜ በዳማችን ፍሳሽና በአጥንታችን *ክስካሽ ወሰናችንን እንዳስከበርን ሁሉ ነገም ከፋኖ ጎን ተሰለን ይኼ ሆዳም ሠራዊትዎን ለማስተንፈስ ዝግጁ ነን፥ ለዚህ ዓላማችን ግብ መምታት* በገንዘባችንም ሆነ በሙያችን ከፋኖ ጎን እንደምንሰለፍ ለኢትዮጵያ እናረጋግጣለን። ፋኖ ከጥንት ጀምሮ የኖረ የአባቶቻችን የአርበኝነት የገድል መጠሪያ ነው። ፋኖ የጎሣ ወይም የሃይማኖት አይደለም ሆኖም አያውቅም

ፋኖ አንግቦ ዓላማ አዲስ ሣይሆን ለዘላለም አባቶቻችን ይዘው ሲታገሉበት የኖሩት ስለሆነ መላ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከጫፍ እስከ ጫፍ እውቀት ያለው በእውቀቱ፣ ጉልበት ያልው በጉልበቱ፣ መዕመናን በፀሎት ከፋኖ ጎን እንዲሰለፉ የኢትዮጵያ ሠራዊት በጽሞና ያሳስብል።

ዘረኝነት ይውደም!!